# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)
# የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ፕሮግራም

## SSL ምንድነው?

- የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ማለት ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መካከል ለሚገኙ ተማሪዎች የስቴት የመመረቂያ መስፈርት/መመዘኛ ነው።
- ተማሪዎች ለማህበረሰቡ በበጎፈቃደኝነት በሚያበረክቱት አገልግሎት ትርጉም ያለው ትምህርት ያገኛሉ።
- የአገልግሎት ትምህርት ስለ ዜጎች/የዜግነት እዉቀት፣ ስለዜጎች ተሳትፎ፣ ስለአካዴሚያዊ ስኬት፣ እና የተማሪዎች ባህርያዊ እና ማህበራዊ እድገትን ያዳብራል/ያበረታታል።
- ቤተሰቦች እና ተማሪዎች የ MCPS SSL ሪሶርሶች ማዕከልን http://bit.ly/SSLHubMCPS እና ይህን ስለ SSLፕሮጀክት ናሙና የሚያስረዳ ቪድኦ http://bit.ly/mcpssslvideo ይመልከቱ!

## የሜሪላንድ (MD) ስቴት እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመዘኛዎች-መስፈርቶች

- የሜሪላንድ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሙሉ ሰባአምስት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት "75 SSL hours" ሠአት ያገኛሉ።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች **5ኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ ካለው ሠመር ጀምሮ በዚህ የመመረቂያ መስፈርት መሠረት መሥራት ይጀምራሉ።** ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከሚጨርሱ ድረስ እየሰሩ ሠዓት ማግኘት ይችላሉ።
- ከ 6 ኛ ክፍል በኋላ በ MCPS የተመዘገቡ ተማሪዎች የ SSL መስፈርትን በማጣጣት-የሚያካክስ እፎይታ ያገኛሉ።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት እንዴት ለማግኘት ይችላሉ?

ተማሪዎች ለምረቃ የሚያስፈልገዉን "75 SSL hours" ለማግኘት የሚችሉት በሁለት መንገድ ነው፡-

1. **ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ኮርሶች በስኬታማነት ሲያጠናቅቁ ሃምሳ የኤስ.ኤስ.ኤል "50 SSL hours" ሠዓቶችን ለማግኘት ይችላሉ።**
   **በክፍል ዳሰሳ/ምርምር እና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች መምህራን ሊመሯቸው ይችላሉ።**

| | |
|---|---|
| 10 ሠዓት | የ6ኛ ክፍል ሳይንስ |
| 10 ሠዓት | የ7ኛ ክፍል እንግሊዝኛ |
| 10 ሠዓት | የ8ኛ ክፍል ማህበራዊ ጥናት |
| 5 ሰአታት | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጤና ኤ |
| + 15 ሠዓት | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር |
| **50 ሠዓት** | **በአጠቃላይ በትምህርት ቤት ክፍሎች - ትምህርቶች ዉስጥ** |

2. **25 የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ከትምህርት ቤት ውጪ (ለትርፍ ባልተቋቋመ ኤጀንሲ)**
   የተረጋገጡ የ MCPS SSL ዕድሎችን ለማግኘት የሞንትጎመሪ የካውንቲ በጎ ፈቃደኛ ማዕከል (MCVC) ድረ-ገጽ (www.montgomeryserves.org) በመጎብኘት ተማሪዎች የ MCPS SSL ድርጅቶችን እና ያሉትን እድሎች መቃኘት ይችላሉ። (ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሁሉም የመመረቂያ ቆብ እና የ "MCPS SSL" ምልክት ይኖራቸዋል። እባክዎ አባሪ በተደረገው ጽሑፍ ላይ የ MCVC ድረ-ገጽ በመፈለግ ፍንጮችን ያግኙ።

   ተማሪዎች በ MCVC ድረ-ገጽ ላይ ራሳቸው የሚፈልጉትን ለትርፍ ያልተቋቋመ ኤጀንሲ (አካባቢያዊ፣ የስቴት ወይም ሀገር አቀፍ) ማግኘት እና መሙላት ይችላሉ **MCPS ቅጽ 560-50 :የግለሰብ ተማሪ የአገልግሎት ትምህርት መጠየቂያ ቅጽ** http://bit.ly/SSLPreApproval እና ለት/ ቤት-ተኮር SSL አስተባባሪ (በትምህርት ዓመቱ ወቅት) ወይም ለ ssl@mcpsmd.org (በሠመር ወቅት) ከአገልግሎት በፊት እንዲፀድቅ መቅረብ አለበት።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት "MCPS SSL" እድሎች በሙሉ መሆን ያለበት፡-

- ለትርፋማነት ያልተቋቋመ የተመዘገበ ኤጀንሲ
- አመሰራረቱ የኃይማኖት ተቋም ያልሆነ/ከሃይማኖት ጋር ግንኙነት የሌለው
- በህዝብ መገልገያ ቦታ
- (በወላጅ ወይም በዘመድ) ክትትል/ቁጥጥር የማይደረግበት
- ለበጎፈቃድ አገልግሎት ብቻ (የማይከፈልበት)
- በቀን ከ8 ሠዓት ያልበለጠ

MCPS SSL

https://bit.ly/SSLOpportunities

## MCPS Form 560-51: የተማሪ አገልግሎት ትምህርት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ http://bit.ly/SSLReflection

ይህ ቅጽ የሚያገለግለው የተማሪን የአገልግሎት ትምህርት ሠዓት ለመመዝገብ እና ለትምህርት ቤት የተማሪን የአገልግሎት ትምህርት አስተባባሪ እንዲገመግም/እንድትገመግም እና በተማሪ SSL ሠዓት ላይ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ የሚሰጥ ነው።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ የ SSL ሠዓት ለማግኘት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ለመወሰን ይህንን የቅደም ተከተል ቻርት ስዕላዊ መግለጫ ተጠቀም(ሚ)።




## ልዩ የሆነ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መስፈርት ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ሁለት አይነት የ SSL ሽልማቶች አሉ።

| ክፍል | ሽልማት |
|---|---|
| **ክፍሎች**<br>**6, 7, እና 8** | **ስለ አገልግሎት ትምህርት ከሱፐርኢንተንደንት የሚሰጥ ሽልማት**<br>(በሚድል ስኩል/መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለ(ች) የተገኘ 75 ሠዓት፣ አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ) |
| **ክፍል**<br>**12ኛ** | **ሽልማት የሚገባው አገልግሎት ሠርተፊኬት/በችሎታ የሚሰጥ አገልግሎት ሠርተፊኬት**<br>(በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመመረቂያ/ሲንየር ዓመት የተገኘ 240 ሠዓት) |

**የ SSL አገልግሎት ቅጾች በሙሉ** በወቅቱ የትምህርት ዓመት እና ከአሁኑ የትምህርት ዓመት ቀደም ባለው በሠመር ለተሰጡ አገልግሎቶች **ያስፈልጋሉ።** ተሞልተው ለትምህርት ቤት የተማሪ የሥራ አገልግሎት ትምህርት አስተባባሪ **ጁን ከመጀመሪያው ዓርብ ቀን በፊት** መቅረብ አለባቸው።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃደኞች ማዕከል ድረ-ገጽ:**
www.montgomeryserves.org

MCPS SSL ድረ -ገጽ:
www.mcps-ssl.org

**ይፈልጉን!**
**@mcpsvolunteers**